



# ፍትሃዊ የቤት አቅርቦት

## እኩል ዕድል ለሁሉም

የዩ.ኤስ የቤቶች እና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት
የፍትሃዊ ቤቶች አቅርቦት እና የእኩል ዕድል ጽ/ቤት

ድረ ገጻችን ይጎብኙ፦ www.hud.gov/fairhousing

Amharic





## ፍትሃዊ የቤት አቅርቦት — እኩል ዕድል ለሁሉም

አሜሪካ በሁሉም ዘርፍ ለሁሉም ሰዎች እኩል ዕድል በመስጠት ትታወቃለች። የዜጎቿ ብዝሃነት እና ሁላችንንም በአንድ የሚይዘን የአንድነት ስሜት የሀገሪቱ መሠረት የሆኑትን የነጻነትና የፍትህ መርሆዎች ይወክላሉ። ለዚያም ነው አዳዲስ ስደተኞች፣ አናሳ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ልጆች ያላቸው ቤተሰቦች እና አካል ጉዳተኞች በህገወጥ መድሎ የተነሳ የፈለጉትን ቤት እንዳያገኙ ሲከለከሉ በጣም የሚረብሸው።

የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD)) የቤት ኪራይና ሽያጭን እንዲሁም የሞርጌጅ ብድሮችን ጨምሮ በሁሉም ከቤት ጋር ተዛማጅ በሆኑ ግብይቶች ላይ መድሎንና ሰዎችን በቤታቸው፣ በአፓርታማ ህንጻዎች እና በኮንዶሚኒየም ህንጻዎች ውስጥ የማሳቀቅ ተግባራትን የሚከለክለውን የፍትሃዊ የቤት አቅርቦት (Fair Housing Act) የሚባል ህግን ያስፈጽማል።

ለኪራይ ቤቶችና ለቤት ባለቤትነት ዕድሎች እኩል መዳረሻ መስጠት የዚህች ሀገር የፌዴራል የቤቶች ፖሊሲ የማዕዘን ድንጋይ ነው። ቤቶችን በዘር፣ በቀለም፣ በመጡበት ሀገር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ ፣ በቤተሰብ ሁኔታ ወይም በአካል ጉዳተኝነት ላይ በመመሥረት ለሰዎች ቤትን ለማከራየት ወይም ለመሸጥ የሚቃወሙ የቤት አቅራቢዎች የፌዴራል መንግስቱን ህግ እየጣሱ ሲሆን የቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንትም ከባድ እርምጃ ይወስድባቸዋል።

በቤት መድሎ ማድረግ ህገወጥ ከመሆኑም በላይ እንደ አሜሪካዊነታችን ከምንመካበት የነጻነት እና የእኩል ዕድል መርሆዎች ጋር ይጣረሳል። ሁሉም ሰው ቤቴ ብሎ የሚጠራውን ቦታ በሚፈልግበት ወቅት በእኩልነት እንደሚስተናገድ ለማረጋገጥ የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል።

### ማውጫ


የፍትሃዊ የቤት አቅርቦት ህግ ........ 1
ምን ዓይነት ቤቶች ይሸፈናሉ? ........ 1
የሚከለከለው ምንድን ነው? ........ 1
አካል ጉዳተኛ ከሆኑ የሚሰጥዎ ተጨማሪ ከለላ ........ 3
ልጆች ላላቸው ቤተሰቦች የሚጥ የቤት ከለላ ........ 4
መብቶችዎ የተጣሱ ከመሰልዎ ........ 6
ቅሬታ ሲያቀርቡ ምን ይሆናል? ........ 9
ቤቱን ቢያስለቅቁኝ ወይም በሽያጭ ላጣው ከሆነ ምን ይሆናል? ........ 11
ያቀረብኩት ቅሬታ ላይ ምርመራ ከተደረገበት በኋላ ምን ይሆናል? ........ 11
በተጨማሪም ........ 13



**የዩ.ኤስ የቤቶች እና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD)**
**451 7th Street, S.W., Washington, D.C. 20410-2000**







## ፍትሃዊ የቤቶች አቅርቦትህግ

የፍህታዊ የቤቶች አቅርቦት ህግ በሚከተሉት ምክንያቶች በቤቶች ላይ የሚደረጉ መድሎዎችን ይከለክላል፦

- በዘር ወይም በቀለም
- በመጡበት ሀገር
- በሃይማኖት
- በጾታ
- በቤተሰብ ሁኔታ (ከወላጆች ወይም ከህጋዊ አሳዳጊዎች ጋር የሚኖሩ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን፣ ነፍሰጡር ሴቶችን እንዲሁም ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች አሳዳጊ የሆኑ ሰዎችን ጨምሮ)
- በአካል ጉዳተኝነት

## ምን ዓይነት የቤቶች አቅርቦቶች ይሸፈናሉ?

የፍትሃዊ የቤቶች አቅርቦት ህግ አብዛኛዎቹን ቤቶች አቅርቦት ዓይነቶችን ይሸፍናል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ህጉ ከአራት የማይበልጡ ክፍሎች ያሏቸው ባለቤቶቹ የሚይዟቸው ህንጻዎች፣ ያለ ደላላ የሚከራዩ ወይም የሚሸጡ አንድ ቤተሰብ ብቻ የሚይዙ ቤቶች እንዲሁም በአባላት ብቻ እንዲያዙ በሚፈቅዱ ድርጅቶችና የግል ክለቦች የሚተዳደሩ ቤቶች በዚህ ህግ አይሸፈኑም።

## የሚከለከለው ምንድን ነው?

በቤት ሽያጭና ኪራይ ወቅት፦ ማንም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በመጡበት ሀገር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ ፣ በቤተሰብ ሁኔታ ወይም በአካል ጉዳተኝነት ላይ ተመሥርቶ የሚከተሉትን ማድረግ አይችልም:

- ቤት አላከራይም ወይም አልሸጥም ማለት
- ቤትን በተመለከተ አልደራደርም ማለት
- ቤቱ እንዳይገኝ ማድረግ
- በሌላ በማንኛውም መንገድ ቤቱ እንዳይያዝ መከልከል
- የቤቱን ሽያጭ ወይም ኪራይ በተመለከተ የተለዩ ውሎችን፣ ሁኔታዎችን ወይም ጥቅሞች መደንገግ
- የተለዩ የቤት አገልግሎቶች ወይም እቃዎች ማቅረብ
- ቤቱ ለመታየት፣ ለኪራይ ወይም ለሽያጭ ክፍት እንዳልሆነ በሃሰት መናገር





- ትርፍ ለማግኘት ሲባል ለቤት ባለቤቶችን የተወሰነ ዘር ያላቸው ሰዎች ወደዚህ አካባቢ መጥተዋል ወይም ሊመጡ ነው የመሳሰሉ ነገሮችን በመንገር ቤታቸውን እንዲሸጡ ወይም እንዲያከራዩ ማሳመን ወይም ለማሳመን መሞከር፣ ወይም
- ማንኛውንም ሰው ከቤት ሽያጭ ወይም ኪራይ ጋር ተዛማጅ በሆነ በማንኛውም ድርጅት ውስጥ፣ ንብረት ወይም አገልግሎት (የዝርዝር አገልግሎቶችን / multiple listing service/ ጨምሮ) ላይ አባል እንዳይሆን ወይም እንዳይሳተፍ መከልከል ወይም እንደ ተደራሽነት፣ አባልነት እና ተሳትፎ በመሳሰሉ ደንቦች ወይም ሁኔታዎች ላይ በማንኛውም ሰው ላይ መድሎ ማድረስ።

በሞርጌጅ ብድር ወቅት፦ ማንም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በመጡበት ሀገር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በቤተሰብ ሁኔታ ወይም በአካል ጉዳተኝነት ላይ ተመሥርቶ የሚከተሉትን ማድረግ አይችልም፦

- የሞርጌጅ ብድር መከልከል
- ብድሮችን የተመለከቱ መረጃዎችን መስጠት መከልከል
- እንደ ወለድ መጠኖች፣ ነጥቦች ወይም ክፍያዎች ያሉ የተለዩ ደንቦችን ወይም ሁኔታዎችን በብድር ላይ መጫን
- የንብረት ዋጋን በመገመት ላይ መድሎ ማድረግ
- ብድርን ለመግዛት መቃወም ወይም
- ብድርን ለመግዛት የተለዩ ደንቦችንና ሁኔታዎችን ተፈጻሚ ማድረግ
- በተጨማሪም  የሚከተሉትን ማድረግ የፍትሃዊ ቤቶች አቅርቦት ህግን መጣስ ነው፦
- የፍትሃዊ ቤቶች አቅርቦት መብቱን እየተጠቀመ ያለን ሰው ወይም መብታቸውን እንዲጠቀሙ ሌሎችን እያገዘ ያለ ሰውን ማስፈራራት፣ ማስገደድ ወይም ማወክ
- የቤት ሽያጭ ወይም ኪራይ ጋር በተገናኘ በዘር፣ በቀለም፣ በመጡበት ሀገር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ ፣ በቤተሰብ ሁኔታ ወይም በአካል ጉዳተኝነት ላይ ተመሥርቶ ምርጫን የሚያመለክት፣ ገደብ የሚያደርግ ወይም መድሎ የሚያደርግ ነገርን ማተም ወይም ማንኛውንም መግለጫ ማውጣት። ይህ መድሎ የሚያደርግ ማስታወቂያን የሚከለክል ድንጋጌ በሌሎች ሁኔታዎች በፍትሃዊ የቤት አቅርቦት ህግ የማይሸፈኑትን አንድ ቤተሰብ ብቻ የሚይዙና በባለቤቶች ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ላይም ተፈጻሚ ይሆናል።
- በቤት ባለቤቱ እና/ወይም በባለይዞታው በዘር፣ በቀለም፣ በመጡበት ሀገር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ ፣ በቤተሰብ ሁኔታ ወይም በአካል ጉዳተኝነት ላይ ተመስርቶ የቤት ባለቤትነት ኢንሹራንስ ሽፋን መከልከል
- በቤት ባለቤቱ እና/ወይም በባለይዞታው በዘር፣ በቀለም፣ በመጡበት ሀገር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ ፣ በቤተሰብ ሁኔታ ወይም በአካል ጉዳተኝነት ላይ ተመስርቶ የቤት ባለቤትነት ኢንሹራንስ  ደንቦች እና ሁኔታዎች ላይ መድሎ ማድረግ





- በቤት ባለቤቱ እና/ወይም በባለይዞታው በዘር ወይም የመሳሰሉት ላይ ተመስርቶ የቤት ባለቤትነት ኢንሹራንስ ሙሉ ሁኔታዎችን በተመለከተ ያሉትን አማራጮች በጠቅላላ በተመለከተ ያሉትን መረጃዎች በሙሉ አለመስጠት
- የቤት ባለቤትነት የኢንሹራንስ ሽፋን በተመለከተ በዘር፣ በቀለም፣ በመጡበት ሀገር፣ በሃይማኖት፣ በጾታ ፣ በቤተሰብ ሁኔታ ወይም በአካል ጉዳተኝነት ላይ ተመስርቶ ምርጫን የሚያመለክት፣ ገደብ የሚያደርግ ወይም መድሎ የሚያደርግ ነገርን ማተም ወይም ማንኛውንም መግለጫ ማውጣት።

## አካል ጉዳተኛ ከሆኑ የሚሰጥዎ ተጨማሪ ከለላ

እርስዎ ወይም ከእርስዎ ጋር የሚኖር ሰው፦

- አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ዋና ዋና የህይወት እንቅስቃሴዎችን እንዳያደርጉ የሚከለክሉ የአካል ጉዳተኝነት ወይም የአዕምሮ ህመም (መስማት፣ መንቀሳቀስና ማየት የተሳነው ከሆነ፣ ካንሰር ወይም ከባድ የአዕምሮ ህመም፣ ኤችአይቪ/ኤድስ ወይም የአዕምሮ እድገት ዝግመትት ጨምሮ) ካለብዎ
- መሰል የአካል ጉዳቶች ኖሮብዎ የሚያውቅ ከሆነ ወይም
- እነዚህን መሰል የአካል ጉዳቶች እንዳለብዎ የሚቆጠር ከሆነ የቤት አቅራቢ የሚከተሉትን ማድረግ አይችልም፦

  - ቤቱን ሙሉ በሙሉ መጠቀም እንዲችሉ የሚያደርጉ ምክንያታዊ ማስተካከያዎችን ቤትዎ ወይም የጋራ መገልገያ አካባቢዎች ላይ በራስዎ ወጪ እንዳያደርጉ መከልከል። (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቤቱ ባለቤት እነዚህን ማስተካከያዎች የሚያደርጉት ቤቱን በሚለቁበት ወቅት ቤቱ በነበረበት ሁኔታ የሚመልሱ ከሆነ ብቻ መፍቀድ ይችላል።)
  - ቤቱን ሌሎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ሰዎች እኩል መጠቀም እንዲችሉ የሚያደርጉ ማስተካከያዎችን በደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ ትግበራዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ እንዳይደረጉ መቃወም።

**ምሳሌ:** "የቤት እንስሳት አይፈቀዱም" የሚባልባቸው ህንጻዎች ማየት የተሳናቸው ተከራዮች የሚመራቸውን ውሻ እንዲይዙ መፍቀድ አለባቸው።

**ምሳሌ:** ለተከራዮች ሰፊና ለማንም ያልተከለለ የመኪና ማቆሚያ የሚሰጡ አፓርታማዎች አንድ እንደልብ መንቀሳቀስ የማትችል አካል ጉዳተኛ ተከራይ ለእርሷ አፓርታማ የሚቀርብና ለመግባት ቀላል የሆነ መኪና ማቆሚያ ቦታ እርሷ ብቻ መጠቀም እንድትችል እንዲመደብላት ያቀረበችውን ጥያቄ ማክበር አለበት።





ነገር ግን የፍትሃዊ ቤቶች አቅርቦት ህግ የሌሎች ሰዎች ጤና ወይም ደህንነት ላይ ቀጥተኛ አደጋ የሚጥል ሰውን ወይም በአሁኑ ወቅት ማንኛውንም ህገ-ወጥ እፆችን ለሚጠቀም ሰው ምንም ዓይነት ከለላ አይሰጥም።

**አዳዲስ ባለብዙ ቤተሰብ ህንጻዎች ላይ ያሉ የተደራሽነት መስፈርቶች፦** ለመጀመሪያ ጊዜ ከማርች 13 ቀን 1991 በፊት የተገባባቸው አራት ወይም ከዚያ በላይ ቤቶች ያላቸውና አሳንሱር ያላቸው ህንጻዎች ውስጥ፦

- የህዝብና የጋራ መገልገያ ቦታዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆን አለባቸው
- ሁሉም በሮችና መተላለፊያዎች ለተሽከርካሪ ወንበሮች (ዊልቼሮች) መተላለፊያ በቂ ስፋት ያላቸው መሆን አለባቸው
- ሁሉም ቤቶች የሚከተሉት ሊኖራቸው ይገባል፦
  - ወደ ቤቱ የሚወስዱና ውስጥ ለውጥ የሚወስድ በቀላሉ የሚገኝ መንገድ
  - በቀላሉ የሚገኙ የመብራት ማብሪያና ማጥፊያዎች፣ መቆጣጠሪየዎች እና ሌሎች የአካባቢ መቆጣጠሪያዎች
  - በኋላ መገጠም የሚያስችል የመደገፊያ ብረቶች እንዲገባባቸው እንዲያመች ተደርገው የተሰሩ የመታጠቢያ ቤት ግድግዳዎች እንዲሁም
  - በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ያሉ ሰዎች ሊጠቀሟቸው የሚችሉ ምግብ ማብሰያ ቤቶችና በታጠቢያ ቤቶች

አንድ አራት ወይም ከዚያ በላይ ቤቶች ያሉት ህንጻ አሳንሱር ከሌለውና ለመጀመሪያ ጊዜ የተገባበት ከማርች 13 ቀን 1991 በኋላ ከሆነ እነዚህ መስፈርቶች ተፈጻሚ የሚሆኑት ለመጀመሪያው ወለል ብቻ ነው።

እነዚህ የአዲስ ባለ ብዙ ቤተሰብ ህንጻዎች ላይ ያሉ የተደራሽነት መስፈርቶች ከዚህ በላይ ጥብቅ የሆኑ የክልል ወይም የአካባቢ ህጎችን አይተኩም።

## ልጅ ላላቸው ቤተሰቦች የሚሰጥ የቤት ከለላ

የፍትሃዊ የቤት አቅርቦት ህግ አንድ ወይም ከዚያ በላይ እድሜያቸው ከ18 በታች የሆኑ ልጆች የሚኖሩበት ቤተሰብ (በቤተሰብ ሁኔታ) ያለው ሰው ላይ መድሎ ማድረግን ህገወጥ ያደርገዋል። የቤተሰብ ሁኔታ ከለላ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ልጆች ከሚከተሉት ጋር ለሚኖሩባቸው ቤተሰቦች ከለላ ይሰጣል፦

- ከወላጅ ጋር፤
- እድሜው ለአቅመ አዳም/ሄዋን ያልደረሰ ልጅ ህጋዊ አሳዳጊነት (ሞግዚትነትን ጨምሮ) ካለው ሰው ጋር፤ ወይም





- ወላጅ ወይም ህጋዊ አሳዳጊ የወከለው፣ ይህ ፈቃድ ከወላጅ ወይም ህጋዊ አሳዳጊ በጽሁፍ የተሰጠ ሲሆን።

ኬቤተሰብ ሁኔታ ከለላ በተጨማሪም ለነፍሰጡር ሴቶችና እድሜው ለአቅመ ሄዋን/አዳም ያልደረሰ ልጅን ህጋዊ አሳዳጊነት የማግኘት ሂደት ላይ ላለ ለማንኛውም ሰው (የጉዲፈቻ ወይም ተንከባካቢ ወላጆችን ጨምሮ) ተፈጻሚ ይሆናል።

**“የአዛውንቶች መኖሪያን” የሚመለከቱ ልዩ ሁኔታዎች፦** የፍትሃዊ የቤት አቅርቦት ህግ የተወሰኑ የአዛውንቶች መኖሪያዎችንና ማህበረሰቦችን ከቤተሰብ ሁኔታ መድሎ ሃላፊነቶች ውጪ ያደርጋል። ከሃላፊነት ውጪ የተደረጉ የአዛውንቶች መኖሪያዎች ወይም ማህበረሰቦች ለአቅመ አዳም/ሄዋን ያልደረሱ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ቤታቸውን መሸጥ ወይም ማከራየትን በህጋዊ መንገድ መቃወም ይችላሉ። ለዚህ “ለአዛውንቶች መኖሪያ ቤት” ከሃላፊነት ማንሻ ብቁ ለመሆን አንድ ቤት ወይም ማህበረሰብ ቤቱ የሚከተሉትን እንደሆነ ማረጋገጥ አለበት፦

- የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት በተለይ አዛውንቶችን ለመርዳት እንዲሆን በወሰነው በማንኛውም የስቴት ወይም የፌዴራል ፕሮግራም መሠረት የተዘጋጀና የሚሰራ (በክልሉ ወይም በፌዴራሉ ፕሮግራም በተገለጸው መሠረት) መሆኑን፤ ወይም
- እድሜያቸው 62 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የሚኖሩበት ወይም ለእነሱ ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን፤ ወይም
- እድሜያቸው 55 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ታስቦ የተዘጋጀና የሚኖሩበት መሆኑን።

“55 ወይም ከዚያ በላይ” ለሆኑ ቤቶች ከሃላፊነት ነጻ መሆን ብቁ ለመሆን አንድ ቤት ወይም ማህበረሰብ የሚከተሉትን መስፈርቶች እያንዳንዳቸውን ማሟላት አለበት፦

- ከቤቶቹ ውስጥ ቢያንስ 80 በመቶ የሚሆኑት ቢያንስ አንድ እድሜው 55 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ሰው ሊኖርበት ይገባል፤ እንዲሁም
- ቤቱ ወይም ማህበረሰቡ “55 እና ከዚያ በላይ” የሆኑ ሰዎችን ለማኖር ታስቦ እንደተዘጋጀ የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችንና አሰራሮችን ማዘጋጀትና መከተል አለበት፤ እንዲሁም
- ቤቱ ወይም ማህበረሰቡ የነዋሪዎችን እድሜ በማረጋገጥ የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት መመሪያ መስፈርቶችን መከተል አለበት።

“የአዘውንቶች መኖሪያ ቤት” ከሃላፊነት ነጻ ማድረጊያ የአዛውንቶች መኖሪያ ተቋማትን ወይም ማህበረሰቦችን በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በአካል ጉዳተኝነት ወይም በመጡበት ሀገር ላይ ተመሥርተው ለሚያደርግ መድሎ ከለላ አይሰጥም።





የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) ከቤት ጋር ተዛማጅ ለሆኑ ማንኛውም ዓይነት መድሎዎች እርስዎን ለማገዝ ዝግጁ ነው። መብቶችዎ የተጣሱ ከመሰልዎ ቅሬታዎን ኦንላየን ማቅረብ ወይም በአቅራቢያዎ ለሚገኘው የቤቶችና ከተማ ልማት ቢሮ ደብዳቤ መጻፍ ወይም ስልክ መደወል ይችላሉ። ለቤቶችና ከተማ ልማት መምሪያ ቅሬታዎችን ለማቅረብ የተጠቀሰው መድሎ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ወይም ካበቃበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ አንድ አመት ጊዜ ቢኖርዎትም በተቻለ መጠን ቶሎ ማቅረብ አለብዎ።

## መብቶችዎ የተጣሱ ከመሰልዎ

**ለቤቶችና ለከተማ ልማት ዲፓርትመንት ምን ይነግራሉ፦**

- ስምዎንና አድራሻዎን
- ቅሬታውን የሚያቀርቡበት ሰው ስም እና አድራሻ (የመልስ ሰጪው)
- የቤቱን አድራሻ ወይም ሌሎች አመላካች ነገሮች
- የተባለውን የመብት ጥሰት አጭር መግለጫ (መብትዎ እንደተጣሰ እንዲያስቡ ያደረግዎትን ክስተት ዝርዝር)
- የተባለው የመብት ጥሰት የተከሰተበት ቀን(ቀናት)

ለማን መጻፍ ወይም መደወል እንዳለብዎ፦ ቅሬታዎን ኦንላየን ያስገቡ ወይም በአቅራቢያዎ ላለ የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት ደብዳቤ ይላኩ ወይም ከፈለጉ ለቢሮው በቀጥታ መደወል ይችላሉ። መስማት የተሳናቸው ሰዎች ወይም የመስማት ችግር ያለባቸውና TTY የሚጠቀሙ ሰዎች ለቢሮዎቹ ከክፍያ ነጻ በሆኑት የፌዴራል መረጃ መቀባበያ አገልግሎት (Federal Information Relay Service) በቁጥር 1-800-877-8339 መደወል ይችላሉ።

ለኮኔክቲከት፣ ሜይን፣ ማሳቹሴትስ፣ ኖው ሃምፕሻር፣ ሮዴ አይላንድ እና ቬርሞንት፦
**ቦስተን ክልላዊ ቢሮ (BOSTON REGIONAL OFFICE)**
(Complaints_office_01@hud.gov)
U.S. Department of Housing and Urban Development
Thomas P. O’Neill Jr. Federal Building
10 Causeway Street, Room 321
Boston, MA 02222-1092
ስልክ (617) 994-8300 ወይም 1-800-827-5005
ፋክስ (617) 565-7313 * TTY (617) 565-5453

ለኒውጀርሲ፣ ኒው ዮርክ፣ ፖርቶ ሪኮ እና ዩኤስ ቨርጂን ደሴቶች፦
**ኒው ዮርክ ክልላዊ ቢሮ (NEW YORK REGIONAL OFFICE)**
(Complaints_office_02@hud.gov)





U.S. Department of Housing and Urban Development
26 Federal Plaza, Room 3532
New York, NY 10278-0068
ስልክ (212) 542-7519 ወይም 1-800-496-4294
ፋክስ (212) 264-9829 * TTY (212) 264-0927

ለዴልዌር /Delaware/፣ ኮሎምቢያ ዲስትሪክት ፣ ሜሪላንድ፣ ፔንሲልቫኒያ፣ ለቨርጂኒያ፣ ለምዕራብ ቨርጂኒያ፦
**ፊላደልፊያ ክልላዊ ቢሮ (PHILADELPHIA REGIONAL OFFICE)**
(Complaints_office_03@hud.gov)
U.S. Department of Housing and Urban Development
The Wanamaker Building
100 Penn Square East
Philadelphia, PA 19107-9344
ስልክ (215) 861-7646 ወይም 1-888-799-2085
ፋክስ (215) 656-3449 * TTY (215) 656-3450

ለአላባማ፣ ፍሎሪዳ፣ ጆርጂያ፣ ኬንተኪ፣ ሚሲሲፒ፣ ኖርዝ ካሮሊና፣ ሳውዝ ካሮሊና እና ለቴነሲ /Tennessee/፦
**አትላንታ ክልላዊ ቢሮ (ATLANTA REGIONAL OFFICE)**
(Complaints_office_04@hud.gov)
U.S. Department of Housing and Urban Development
Five Points Plaza
40 Marietta Street, 16th Floor
Atlanta, GA 30303-2808
ስልክ (404) 331-5140 ወይም 1-800-440-8091 x2493
ፋክስ (404) 331-1021 * TTY (404) 730-2654

ለኢሊዮኒስ /Illinois/፣ ኢንዲያና፣ ሚቺጋን፣ ሚኒሶታ፣ ኦሃዮ እና ለዊስከንሲን፦
**ቺካጎ ክልላዊ ቢሮ (CHICAGO REGIONAL OFFICE)**
(Complaints_office_05@hud.gov)
U.S. Department of Housing and Urban Development
Ralph H. Metcalfe Federal Building
77 West Jackson Boulevard, Room 2101
Chicago, IL 60604-3507
ስልክ 1-800-765-9372
ፋክስ (312) 886-2837 * TTY (312) 353-7143





ለአርካንሳስ /Arkansas/፣ ለሉይዚያና /Louisiana/፣ ኒው ሜክሲኮ፣ ኦክላሆማ እና ለቴክሳስ፦
**ፎርትወርዝ ክልላዊ ቢሮ (FORT WORTH REGIONAL OFFICE)**
(Complaints_office_06@hud.gov)
U.S. Department of Housing and Urban Development
801 Cherry Street
Suite 2500, Unit #45
Fort Worth, TX 76102-6803
ስልክ (817) 978-5900 ወይም 1-888-560-8913
ፋክስ (817) 978-5876/5851 * TTY (817) 978-5595

ለአዮዋ፣ ካንሳስ፣ ሚሶሪ እና ለነብራስካ፦
**ካንሳስ ክልላዊ ቢሮ (KANSAS CITY REGIONAL OFFICE)**
(Complaints_office_07@hud.gov)
U.S. Department of Housing and Urban Development
Gateway Tower II
400 State Avenue, Room 200, 4th Floor
Kansas City, KS 66101-2406
ስልክ (913) 551-6958 ወይም 1-800-743-5323
ፋክስ (913) 551-6856 * TTY (913) 551-6972

ለኮሎራዶ፣ ሞንታና፣ ኖርዝ ዳኮታ፣ ሳውዝ ዳኮታ፣ ኡታህ /Utah/ እና ሚዮሚንግ፦
**ዴንቨር ክልላዊ ቢሮ (DENVER REGIONAL OFFICE)**
(Complaints_office_08@hud.gov)
U.S. Department of Housing and Urban Development
1670 Broadway
Denver, CO 80202-4801
ስልክ (303) 672-5437 ወይም 1-800-877-7353
ፋክስ (303) 672-5026 * TTY (303) 672-5248

ለአሪዞና፣ ካሊፎርኒያ፣ ሃዋይ እና ኔቫዳ / Nevada/
**ሳን ፍራንሲስኮ ክልላዊ ቢሮ (SAN FRANCISCO REGIONAL OFFICE)**
(Complaints_office_09@hud.gov)
U.S. Department of Housing and Urban Development
600 Harrison Street, Third Floor
San Francisco, CA 94107-1387
ስልክ 1-800-347-3739
ፋክስ (415) 489-6558 * TTY (415) 489-6564





**ለአላስካ፣ ኢዳሆ /Idaho/፣ ኦሪገን እና ዋሺንግተን፦**
**ሲያትል ክልላዊ ቢሮ (SEATTLE REGIONAL OFFICE)**
(Complaints_office_10@hud.gov)
U.S. Department of Housing and Urban Development
Seattle Federal Office Building
909 First Avenue, Room 205
Seattle, WA 98104-1000
ስልክ (206) 220-5170 ወይም 1-800-877-0246
ፋክስ (206) 220-5447 * TTY (206) 220-5185

በአቅራቢያዎ የሚገኘውን ቢሮ አነጋግረውም ጥያቄ ካለዎት - በተጨማሪም የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንትን በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይችላሉ፦

U.S. Department of Housing and Urban Development
Office of Fair Housing and Equal Opportunity
451 7th Street, S.W., Room 5204
Washington, DC 20410-2000
ስልክ 1-800-669-9777
ፋክስ (202) 708-1425 * TTY 1-800-927-9275
www.hud.gov/fairhousing

አካል ጉዳተኛ ከሆኑ፦ የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት በተጨማሪም የሚከተሉትን ያቀርባል፦

- መስማት ለተሳናቸውና የመስማት ችግር ላለባቸው ተጠቃሚዎች የTTY ስልክ (በአቅራቢያዎ ለሚገኙ የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት ቢሮዎች ከላይ ያለውን ዝርዝር ይመልከቱ)
- አስተርጓሚዎች፣ ቴፖችና የብሬይል መሳሪያዎች
- ቅጾችን በማንበብና በመሙላት ወቅት እገዛ

## ቅሬታ ሲያቀርቡ ምን ይሆናል?

ቅሬታዎ በፍትሃዊ የቤት አቅርቦት ህግ መሠረት ተቀባይነት ሲያገኝ ይህንኑ የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት በጽሁፍ ያሳውቅዎታል። በተጨማሪም የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) የሚከተሉትን ያደርጋል፦

- ሙብት የመጣስ ቅሬታ ለቀረበበት ሰው (መልስ ሰጪ) ቅሬታ እንደቀረበበት ያሳውቅና ለቅሬታው የጽሁፍ መልስ እንዲሰጥ ጊዜ ይሰጠዋል።





- ቅሬታዎን ይመረምርና የፍትሃዊ የቤት አቅርቦት ሕግ እንደተጣሰ የሚያሳምኑ ምክንታዊ መነሻዎች እንዳሉና እንደሌሉ ይወስናል።
- የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) ምርመራውን ማመልከቻውን ካስገቡበት ቀን ጀምሮ በ100 ቀናት ውስጥ ማጠናቀቅ የማይችል ከሆነ ለእርስዎ ያሳውቅና የመዘግየቱን ምክንያት ያስረዳል።

**የፍትሃዊ የቤት አቅርቦት ህግ እርቅ፦** የቅሬታው ምርመራ በሚደረግበት ወቅት የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት እርስዎና መልስ ሰጪው ቅሬታውን በፈቃደኝነት በእርቅ ስምምነት እንድትፈቱት እድሉን ማመቻቸት ይጠበቅበታል።

የእርቅ ስምምነት ለእርስዎ መፍትሄን ከመስጠት በተጨማሪ መልስ ሰጪው ከአሁን በኋላ መድሎ እንዳይፈጽም በማድረግ የህዝብ ጥቅምን ያስከብራል። እርስዎና መልስ ሰጪው አንድ ጊዜ የእርቅ ስምምነት ከፈረሙ በኋላና የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት ስምመነቱን ካጸደቀ በኋላ ዲፓርትመንቱ ቅሬታዎ ላይ ምርመራ ማድረጉን ያቆማል። መልስ ሰጪው የእርቅ ስምምነቱንም እንዳላከበረና እንደጣሰ የሚያምኑ ከሆነ ቅሬታዎን ሲመረምር ለነበረው የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት ይህንኑ ቶሎ ማሳወቅ አለብዎት። የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንቱ መልስ ሰጪው ስምምነቱን እንደጣሰው የሚያሳይ በቂ ምክንያት እንዳለ ካመነ የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት መልስ ሰጪው የስምምነቱን ድንጋጌዎች እንዲያከብር እንዲገደድ በፌዴራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤቶች ክስ እንዲያቀርብበት ለዩ.ኤስ. የፍትህ ዲፓርትመንት ጥያቄ ያቀርባል።

**ቅሬታዎችን ወደ ስቴት ወይም አካባያዊ የፍትሃዊ የቤቶች አቅርቦት ኤጀንሲዎች ማስተላለፍ፦** የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት የእርስዎ የስቴት ወይም አካባቢያዊ የመንግስት ፍትሃዊ የቤቶች አቅርቦት ኤጀንሲ የሲቪል መብቶች ህግ ወይም ከፍትሃዊ የቤቶች አቅርቦት ህግ ጋር "ተመጣጣኝ" የሆኑ መብቶችን፣ ከሳዎችንና ከለላዎችን የሚሰጡ ህጎችን እንደሚያስፈጽም ካረጋገጠ የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንቱ ወዲያውኑ ቅሬታዎን ለዚህ ኤጀንሲ እንዲመረምረው ማስተላለፍ ያለበት ሲሆን ያስተላለፈው መሆኑንም ለእርስዎ ቶሎ ማሳወቅ አለበት። የስቴት ወይም አካባቢያዊ ኤጀንሲው ቅሬታዎን "ተመጣጣኝ" በሆነው ክልላዊ ወይም አካባቢያዊ የሲቪል መብቶች ህግ ወይም ሌሎች ህጎች መሠረት ይመረምረዋል። የስቴት ወይም አካባቢያዊ የሕዝብ ፍትሃዊ ቤቶች አቅርቦት ኤጀንሲው ቅሬታዎ በቤቶችና በከተማ ልማት ዲፓርትመንት ከተላለፈለት ጊዜ ጀምሮ ባሉ 30 ቀናት ውስጥ ምርመራውን መጀመር አለበት። ይህ የማይደረግ ከሆነ የቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንቱ ቅሬታውን መልሶ መውሰድ ("ዳግም መጀመር") እና በፍትሃዊ የቤቶች ድልድል ህግ መሰረት ምርመራ ማካሄድ ይችላል።





## ከቤቴ ቢያስወጡኝ ወይም በሽያጭ ላጣው ከሆነ ምን ይሆናል?

የፍትሃዊ ቤቶች አቅርቦት ህግ በመጣሱ ምክንያት የሚደርስን ከባድ ችግርን ለማስቆም ወይም ለመከላከል አስቸኳይ እገዛ ካስፈለግዎ የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት ወዲያውኑ ቅሬታውን እንዳቀረቡ ሊያግዝዎ ይችላል። የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት የዩ.ኤስ. የፍትህ ዲፓርትመንት በፌዴራል የዲስትሪክት ፍርድ ቤት የጊዜያዊ የማስቀሚያ ትዕዛዝ (Temporary Restraining Order (TRO)) የሚያስጥ ከዚያም የቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት የሚያደርገው ምርመራ እስኪጠናቀቅ ድረስ የሚቆይ እግድ (Preliminary Injunction) እንዲሰጥ የሚያስችል አቤቱታ እንዲያቀርብ ስልጣን ሊሰጠው ይችላል። የፌዴራል ዳኛው በሚከተሉት ሁኔታዎች መልስ ሰጪው ላይ ጊዜያዊ የማስቀሚያ ትዕዛዝ (TRO) ወይም እግድ (Preliminary Injunction) በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊሰጥ ይችላል፦

- የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት ምርመራው ሳይደረግ ቢቀር የቤት መብቶች ላይ መመለስ የማይቻል (የማይቀለበስ) ጉዳት የሚደርስ ከሆነ፤ እና
- መልስ ሰጪው የፍትሃዊ ቤቶች አቅርቦት ህግን እንደጣሰ የሚያሳይ በቂ ማስረጃ ሲኖር።

**ምሳሌ:** አንድ የቤት ባለቤት ቤቱን ሊሸጥ ከተስማማ በኋላ ገዢዎቹ ጥቁር እንደሆኑ ሲያውቅ ቤቱን ከገበያ ውስጥ ካወጣው በኋላ ወዲያውኑ መልሶ የሚሸጥ ቤት መሆኑን የሚያሳይ ዝርዝር ውስጥ ያካትተዋል። ገዢዎቹ የመድሎ ቅሬታ ለቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት ያቀርባሉ። በዚህ ጊዜ የቤቶችና የከተማ ልማት መምሪያው ምርመራውን እስከሚጨርስ ድረስ ባለቤቱ ቤቱን ለሌላ ሰው እንዳይሸጠው የሚከለክል እግድ እንዲሰጠው ለፌዴራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤት እንዲያመለክት ለዩ.ኤስ. ፍትህ ዲፓርትመንት ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

## ከቅሬታው ምርመራ በኋላ ምን ይሆናል?

**የምክንያታዊ መነሻ፣ የመድሎ ክስ ውሳኔ እና ምርጫ ፡** ያስገቡት ቅሬታ በሚጠናቀቅ ጊዜ የቤቶች አቅርቦትና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) በምርመራው ጊዜ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማጠቃለል የመጨረሻ የምርመራ ሪፖርት ያዘጋጃል። የቤቶች አቅርቦትና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) መላሹ(ሾቹ) በእርስዎ ላይ መድሎ ማድረጋቸውን ለማመን የሚያስችል ምክንያት አለ ብሎ ከወሰነ HUD የአሳማኝ ምክንያት ውሳኔ እና በመላሹ(ሾቹ) ላይ የመድሎ መፈጸም ክስ ይሰጣል። እርስዎ እና መላሹ(ሾቹ) ክሱ በHUD አስተዳደራዊ ሕግ ዳኛ (ALJ) ወይም በፌዴራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤት እንዲታይላችሁ ለመወሰን የክሱ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሃያ (20) ቀናት አላችሁ።





**የHUD የአስተዳደራዊ ሕግ ዳኛ ችሎት፦** የ20-ቀኑ የመምረጫ ጊዜ ከማለፉ በፊት እርስዎም ሆኑ መልስ ሰጭው በፌደራል ፍርድ ቤት እንዲታይላችሁ ካልመረጣችሁ የቤቶች እና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) ወዲያውኑ ችሎቱ በHUD የአስተዳደራዊ ሕግ ዳኛ (ALJ) እንዲሆን ቀን-ቀጠሮ ይይዛል። የALJ ችሎት ክስ የቀረበበት መድሎ ተፈጸመ የተባለበት አካባቢ የሚካሄድ ይሆናል። በALJ ችሎት ጊዜ እርስዎ እና ተከሳሹ(ሾቹ) በአካል የመቅረብ፣ በሕግ አማካሪ የመወከል፣ ማስረጃ የማቅረብ፣ ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ እና ማስረጃዎችን ለማፈላለግ የፍርድ ቤት ማዘዣ የመጠየቅ መብት አላችሁ። የHUD ጠበቃዎች በALJ ችሎት ላይ ምንም ክፍያ ሳይጠይቁዎት ጥብቅና ይቆሙልዎታል። ሆኖም ግን በክርክሩ ላይ ጣልቃ ለመግባት እና የራስዎን ጠበቃ ለማቆም ሊመርጡ ይችላሉ። በችሎቱ ማጠቃለያ ላይ የHUD ALJ በተገኙ እውነታዎች እና በሕግ መደምደሚያዎች ላይ በመመርኮዝ ውሳኔ ይሰጣል። የHUD ALJ ተከሳሹ(ሾቹ) የፍትሃዊ ቤት አቅርቦት ደንብን ተላልፈዋል ብሎ ከደመደመ ተከሳሹ(ሾቹ) የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ሊታዘዙ ይችላሉ፦

- የኪስ ወጭዎችን እና የስሜት መጎዳትን ጨምሮ ለደረሱ ጉዳቶች ካሳ እንዲከስ/ሱ
- ቋሚ የእገዳ ትዕዛዝ (permanent injunctive relief) መስጠት
- ተገቢውን ፍትሃዊ መፍትሄ መስጠት (ለምሳሌ ቤቱን እርስዎ እንዲያገኙት ማድረግ)
- ተመጣጣኝ የሆነ የጠበቃ ክፍያዎችዎን መክፈል
- የቤቶች እና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) የሕዝብ መብትን ለማስከበር ማጣራት ላደረገበት የፍትሃ-ብሔር ቅጣት መክፈል። ከፍተኛዎቹ የፍትሃ-ብሔር ቅጣቶች፦ $16,000፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ደንብ ጥሰት፤ $37,500 በአለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ሌላ የተፈጸመ ጥሰት ካለ፤ እና $65,000 ባለፉት ሰባት ዓመታት ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የቀደሙ ጥሰቶች የተከሰቱ ከሆኑ።

**በፌዴራል ዲትሪክት ፍርድ ቤት ውስጥ የፍትሃ-ብሔር ችሎት፦** እርስዎ ወይም መልስ ሰጪው ቅሬታዎ በፌዴራል የፍትሐ ብሔር ችሎት እንዲታይ ከመረጣችሁ የቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት ጉዳዩን ለዩኤስ የፍትህ ዲፓርትመንት ማስተላለፍ አለበት። የዩ.ኤስ. የፍትህ ዲፓርትመንት እርስዎን በመወከል የተባለው መድሎ የተፈጸመበት ዲስትሪክት ውስጥ ባለ የዩ.ኤስ. ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ውስጥ የፍትሃ-ብሔር ክስ ይመሠርታል። በክሱ ላይ ጣልቃ መግባትና በራስዎ ጠበቃ ለመከራከርም ይችላሉ። እርስዎ ወይም መልስ ሰጪው ጉዳዩ በፍርድ ሸንጎ (a jury trial) እንዲታይ የመጠየቅ፣ በአካል የመቅረብ፣ በጠበቃ የመወከል፣ ማስረጃ የማቅረብ፣ ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ፣ እንዲሁም ማስረጃ እንዲቀርብ አስገዳጅነት ያለው መጥሪያ እንዲሰጥ የመጠየቅ መብት አላችሁ።





የፌዴራል ፍርድ ቤቱ ለእርስዎ ከፈረደልዎ ዳኛው ወይም ሸንጎው መልስ ሰጪው(ዎቹ) የሚከተሉትን እንዲፈጽሙ ሊያዝ ይችላል፦

- ከኪስዎ ያወጡትን ወጪዎችና የስነ ልቦና ጉዳቶች ጨምሮ ለደረሰብዎት ጉዳት ካሳ እንዲከፍል
- ቋሚ የሆነ የእገዳ ትዕዛዝ /permanent injunctive relief/ መስጠት
- ተገቢውን ፍትሃዊ መፍትሄ መስጠት (ለምሳሌ ቤቱን እርስዎ እንዲያገኙት ማድረግ)
- ምክንያታዊ የሆነ ለጠበቃ ያወጡትን ወጪ እንዲከፍል ማድረግ
- የቅጣት ክፍያዎችን እንዲከፍልዎት ማድረግ

ምንም ምክንያታዊ የሆነ መነሻ እንደሌለ ሲወሰንና ጉዳዩ ሲዘጋ፦ የቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት መልስ ሰጪው(ዎቹ) ህጉን እንደጣሱ የሚያመለክት ምንም ምክንያታዊ መነሻ እንደሌለ ሲያውቅ ምንም ምክንያታዊ መነሻ የለም በሚል ክሱን ይዘጋዋል። የቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት ለእርስዎ እና ለመልስ ሰጪው(ዎቹ) ጉዳዩ መዘጋቱን በደብዳቤ የሚያሳውቅ ሲሆን የመጨረሻ የምርመራ ሪፖርቱን ቅጂ እንዲደርስዎ መጠየቅ ይችላሉ።

ምንም ምክንያታዊ መነሻ የለም የሚለው ውሳኔን በድጋሚ ማየት፦ የፍትሃዊ የቤቶች አቅርቦት ህግ በቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት የተዘጉ ቅሬታዎችን በተመለከተ ምንም ዓይነት መደበኛ የይግባኝ አማራጭ አይሰጥም። ነገር ግን ቅሬታዎ ምንም ምክንያታዊ መነሻ የለም ተብሎ ከተዘጋ ውሳኔው በድጋሚ እንዲታይ ለሚከተለው አካል በጽሁፍ ማቅረብ ይችላሉ። እርሱም ለDirector, FHEO Office of Enforcement, U.S. Department of Housing and Urban Development, 451 7th Street, SW, Room 5206, Washington, DC 20410-2000 ይሆናል።

## በተጨማሪም

የግል ክስ መመስረት ይችላሉ፦ መጀመሪያ በቤቶችና የከተማ ልማት ዲፓርትመንት ቅሬታ ሳያቀርቡ በግል የፍትሃ-ብሔር ክስ መመሥረት ይችላሉ። የተጠቀሰው የመድሎ ድርጊት ከተፈጸመበት ቀን አንስቶ በሁለት (2) ዓመት ውስጥ ክስ መመስረት ይችላሉ።

በቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት ቅሬታ ቢያቀርቡና ቅሬታዎ ቢዘጋም የፍትሃዊ ቤቶች አቅርቦት ህጉ መልስ ሰጪው(ዎቹ) ላይ የግል የፍትሃ-ብሔር ክስ በፌዴራል ዲስትሪክት ፍርድ ቤቶች እንዲመሠርቱ መብት ይሰጥዎታል። የቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት ክስዎን እየመረመረ የወሰደው ጊዜ





የሁለት ዓመት ክስ የማቅረቢያ (ፋይል የማድረጊያ)ጊዜ ውስጥ አይቆጠርም ወይም አይደመርም። ክሱን የሚመሠርቱት በራስዎ ወጪ ነው። ነገር ግን ጠበቃ መቅጠር ካልቻሉ ፍርድ ቤቱ አንድ ጠበቃ ሊያቆምልዎት ይችላል።
ምንም እንኳን የቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት ቅሬታዎን እያየ ቢሆንም የሚከተሉት ካልሆኑ በስተቀር አሁንም መልስ ሰጪው ላይ የግል የፍትሃ-ብሔር ክስ መመሥረት ይችላሉ (1) ቅሬታዎን በእርቅ ለመፍታት የቤቶችና ከተማ ልማት መምሪያን የእርቅ ስምምነት ያልፈረሙ ከሆነ ወይም (2) የቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት አስተዳደራዊ ዳኛ ለቅሬታዎ አስተዳደራዊ ክስ መስማት ሂደት ካልጀመረ።

የቤቶች አቅርቦትን በተመለከተ የሚፈጸሙ መድሎዎችን ለማስቀም የሚረዱ ሌሎች የህግ ሰነዶች፦


- የአስተዳደራዊ ህግ ዳኛውን ትዕዛዝ ካልተከበረ የቤቶችና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት ከዩናይትድ ስቴትስ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጊዜያዊ የሆነ እገዳ፣ ትዕዛዙን በሃይል ማስፈጸም ወይም የመከልከያ ትዕዛዝ እንዲሰጥ መጠየቅ ይችላል።
- የቤቶች አቅርቦትን በተመለከተ ተደጋጋሚ የሆነ መድሎ እንዳለ ወይም መድሎ ያለበት አሰራር እየተከናወነ እንዳለ ለማመን ምክንያታዊ መነሻ ሲኖረው ጠቅላይ አቃቢ ህግ በፌዴራል የዲትሪክት ፍርድ ቤት ክስ ሊመሠርት ይችላል።



# ማስታወሻዎች



# ማስታዎሻዎች



# ማስታወሻዎች



# ማስታወሻዎች

## ለተጨማሪ መረጃ

የዚህ ብሮሹር ዓላማ በፍትሃዊ የቤቶች አቅርቦት ዙሪያ ያሉዎትን መብቶች አጠቃሎ ማቅረብ ነው። የፍትሃዊ ቤቶች አቅርቦት ህግ እናየቤቶች እና የከተማ ልማት ዲፓርመንት (HUD) ደንቦች የበለጠ ዝርዝር እና ቴክኒካዊ መረጃዎችን ይዘዋል። የህጉን ወይም የደንቦቹን ቅጅ ማግኘት ከፈለጉ በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የቤቶች እና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) ፍትሃዊ የቤቶች አቅርቦት ጽ/ቤትን ያነጋግሩ። የቤቶች እና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) ፍትሃዊ የቤቶች አቅርቦት ጽ/ቤቶችን ዝርዝር ከገጽ 7-10 ይመልከቱ።.



**ከቤቶች እና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት (HUD) ጋር ይገናኙ።**

ከቤቶች እና ከተማ ልማት ዲፓርትመንት ቢሮ
Room 5204
ዋሽንግተን ዲሲ 20410-2000

U.S. DEPARTMENT OF HOUSING AND URBAN DEVELOPMENT

02305

EQUAL HOUSING OPPORTUNITY

HUD-1686-1-FHEO
2011

ድረ ገጻችን ይጎብኙ፦ www.hud.gov/fairhousing